


Ethiopia: ሰበር መረጃ - ጎንደር በመትረየስ እና በፈንጂ ስትታመስ አደረች - ለምን? | ዝርዝሩን ይዘነዋል | Zehabesha News | Gonder
Zehabesha Official  March 20, 2020

## አህያውን ቢፈሩ መደላድሉን

ኧረ ማነው፣ ይህን ግፍ የሰራው?
ጎንደርንስ ለምን ነው በፍርሃት የተመለከተው?
ሕፃናትን፣ ሽማግሌ፣ ባልቴቶችንና እናቶችን፤
በጎንደር ከተማና በአካባቢው የጥይት ባሩድ ሲያፈስ ያደረው፤
ወንበዴና ነፍስ ገዳዩ ማነው?
በመትረየስ ለመደብደብስ
ወስኖና ያዘዘው ማን ይሆን።
**አህያውን ቢፈሩ መደላድሉን፤**
**ተው አታስታውሱኝ ሰላሣ አመታትን።**
ሴት ልጅን ደፍሮ ውንድ ልጅን
እያኮላሸ በጨለማ አጉሮ፣
ጎሳውን ወርቅ ብሎ፣
አሸንድዬ ዬኔ ነው፣ አንተ አፍህን ዝጋው፣
ያን ባታደርግ ግን ቤትህ መቃበር ነው።
ብሎ ሲያስፈራራ በዱር በገደሉ
ሴት ወንድ ወጣቱ ግን ያን ያልተቀበለው፤
እምቢ አሻፈረኝ ነፃነት ወይም ሞት፤
በማለት፣ደፍሮ በወጣበት፣
ባዶ እጁን በማንሳት፣
እሪ የሰው ያለህ ኡኡ፣ አቤት፣ አቤት
ብሎም በተጣራ፤
እንዴት በጎንደር ሕዝብ
የቦምብ ናዳ ሌት ከቀን ይዘራ?
**አህያውን ቢፈሩ መደላድሉን፤**
**ተው አታስታውሱኝ ሰላሣ አመታትን።**
ኧረ ማነው፣ ይህን ግፍ የሰራው?
ጎንደርንስ ለምን ነው በፍርሃት የተመለከተው?

© ለምለም ፀጋው፣ March 20, 2020

]